በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በኢትዮጵያ ትራንስፖርት ባለስልጣን

# በህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ እና አስተዳደር ላይ የተከናወነ የክትትል

# ኦዲት ሪፖርት

ጥር 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**ማውጫ**

ክፍል 1 ....... 3
መግቢያ ....... 3
የባለሥልጣን መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር ....... 3
የክትትል ኦዲቱ (Follow up audit) ዓላማ ....... 5
የክትትል ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ....... 5
ለክትትል ኦዲቱ የተለየው አካባቢ/ Follow up Audit Identified Area/ ....... 6
የክትትል ኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫና መመዘኛ መስፈርቶች ....... 6
ክፍል ሁለት ....... 7
በክትትል ኦዲቱ (Follow up audit) የተገኙ ግኝቶች ....... 7
ክፍል ሶስት ....... 26
መደምደሚያ ....... 26
ክፍል አራት ....... 29
በክትትል ኦዲት(Follow up audit) የታዩ ትኩረት የሚሹ የማሻሻያ ሀሳቦች ....... 29
አባሪ 1 ....... 31

# ክፍል 1

## መግቢያ

1. በህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሰማሩትንና የሚሰሩትን ፈቃድ የሚሰጥ፣ ስምሪታቸውን የሚቆጣጠር፣ የትራንስፖርት ማህበር ሲቋቋም የሚፈቅድ፣ ለአገር አቋራጭ ከፍተኛ አውቶቢሶች በጊዜው በነበረው አደረጃጀት ስርዓት መሰረት ወደ 14ቱም የጠቅላይ ግዛቶች ዋና ከተሞች እንዲሰማሩ የመስመር ድልድል የሚያዘጋጅ፣ እንዲሁም ቻርተርድ ባልሆኑ ከተሞችም የከተማ ትራንስፖርት/ታክሲ/ አገልግሎትን የሚቆጣጠር መ/ቤት በማስፈለጉ በትዕዛዝ ቁጥር 49/1960 መሰረት በአዋጅ ቁጥር 256/61 አንድ ራሱን ችሎ የሚተዳደርና ተጠሪነቱም ለፖስታ፣ ለቴሌኮሚኒኬሽንና ቴሌፎን ሚኒስቴር የሆነ መ/ቤት ተቋቋመ ፡፡ የባለሞተር ተሽከርካሪዎች ፍጥነት ወሰንን የሚወስን ደንብ ደግሞ በደንብ ቁጥር 361/1961 እንዲወጣ ተደረገ ፡፡
2. ከ 1966 ዓ.ም የመንግስት ለውጥ በኋላ መ/ቤቱ " የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን" በመባል በአዋጅ ቁጥር 107/69 ተቋቁሟል ፡፡ ተጠሪነቱም ለትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር እንዲሆን ተደረገ ፡፡
3. በ 1983 ዓ.ም የሽግግር መንግስት ከተመሰረተ በኋላ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 14/1984 እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል ፡፡ ከዚያም በኋላ በ 1997 ዓ.ም አዲስ በወጣው አዋጅ 468/97 መሰረት መ/ቤቱ እንደ አዲስ በመዋቀር የትራንስፖርት ባለሥልጣን በመባል ተጠሪነቱ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር /ለቀድሞው ለትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር/ ሆኖ ተቋቁሟል ፡፡

# የባለሥልጣን መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

4. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 468/97 መሰረት ከተሰጡት ስልጣንና ተግባር መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

- ትራንስፖርትን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሀሳቦችን አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ማቅረብ፤ ሲፈቀዱ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ደህንነቱ የተረጋገጠ ፣ ቀልጣፋና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት መኖሩን መከታተል፣ ትራንስፖርትን የሚመለከቱ የመንግስት ፖሊሲዎችንና ህጎችን እንዲሁም ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሥራ ላይ ማዋልና ማስፈፀም፣

- በአገር ደረጃና በዓለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት መስመሮች እንዲዘረጉ ማድረግ፣
- የተቀናጀ የህዝብና የዕቃ ትራንስፖርት ስርዓት እንዲስፋፋ ማድረግ፤ መንገደኞች፣ ዕቃዎችና ፖስታዎች በንግድ ትራንስፖርት ስለሚጓጓዙበት ሁኔታ መመሪያ ማውጣትና አፈፃፀሙን መከታተል ፣
- ትራንስፖርትን የሚመለከቱ ማናቸውም መረጃዎችና ስታትስቲኮችን በቋሚ ሁኔታ መሰብሰብና ማጠናቀር፣
- ስለ ትራንስፖርት አገልግሎት እንደ አግባቡ የስልጠናና የምክር አገልግሎት መስጠት፤ እንደ አስፈላጊነቱም የማሰልጠኛ ተቋሞችን ማቋቋምና ማካሄድ፣
- ትራንስፖርት በማናቸውም ረገድ ስለሚያድግበት ሁኔታ ጥናቶች ማካሄድ፣ እንዲካሄድ ማበረታታት እንዲሁም ፕላንና ፕሮግራም ማዘጋጀት፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ማድረግ፣
- በህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ በተሰማሩ ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና ማህበሮች የገበያ እጦት ሲያጋጥም ወይም በተገለጋዩ ህብረተሰብ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትና ፍላጎት መጣጣሙን ማረጋገጥና ስምሪቱን ፍትሀዊ እንዲሆን ማድረግ፣ ከባቡሮች ስለሚወጣው ጭስ፣ ጋዝና ትነት ስለመሳሰሉት ከሀገሪቱ አቅምና ከዓለም አቀፍ መመዘኛዎች ጋር የተገናዘበ ደረጃ አዘጋጅቶ ማቅረብ፤ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን መከታተል፣
- ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ማስወሰንና መሰብሰብ፣ በህዝብ የንግድ መንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ በተሰማሩት ግለሰቦች ፣ ድርጅቶችና ማህበሮች የገበያ እጦት ሲያጋጥም ወይም በተገለጋዩ ህብረተሰብ የትራንስፖርት አገልግሎት እጥረት ሲከሰት ክትትል ማድረግ፣ እንዲሁም የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትና ፍላጎት መጣጣሙን ማረጋገጥና ስምሪቱ ፍትሀዊ እንዲሆን ማድረግ፣
- የቢሮዎችን አቅም ለማጎልበት አመቺ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ በመንገዶች የሚጠቀሙ ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ከሚሰጡት አገልግሎት አይነት ሊኖራቸው የሚገባውን የደህንነት መሳሪያዎች ክብደትና መጠናቸውን እንዲሁም የተሳፋሪን ብዛትና የጭነት ክብደትና መጠናቸውን መወሰን በዚሁ መሰረት ምዝገባ እንዲካሄድ የማረጋገጫ ሰርተፊኬት መስጠት፣
- በሀገር አቋራጭና ዓለም አቀፍ የንግድ ሰዎች ማመላለሻ ሥራ ላይ ለሚሰሩ ሰዎችና ድርጅቶች የሙያ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠትና መከታተል፣
- በሀገር አቋራጭና በዓለም አቀፍ የንገድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ወይም ንብረታቸው የዲፕሎማቲክ፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከአንድ ክልል ወይም የፌዴራል መንግስት የሆኑ ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን መመዝገብና የቴክኒክ ምርመራ ማካሄድ፤ እንዲሁም መከታተል፣

- በአገር አቋራጭና በዓለም አቀፍ የህዝብ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ድርጅቶች ወይም ማህበራት የሚያስከፍሉትን ታሪፍ ለሚሰጡት አገልግሎት ማግኘት ስለሚገባቸው ጥቅምና የተጠቃሚውን የመክፈል አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ማስፀደቅ፣
- ስለተሽከርካሪዎች አመዘጋገብና የቴክኒክ ምርመራ መመሪያ ማውጣትና መከታተል፣
- ለህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚውሉ መናህሪያዎች ደረጃና መመዘኛ/ስፔስፊኬሽን/ ማውጣትና መከታተል፣
- በአገር አቋራጭና በዓለም አቀፍ የህዝብ ማመላለሻ ሥራ ለሚሰማሩ ተሽ ከርካሪዎች ማህበራት የሚያቀርቡትን የስምሪት ፕሮግራም ማፅደቅ፣ ካልቀረበለትም ራሱ ማዘጋጀትና ለዚሁ የወጣውን የዲስፕሊን መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በገበያ ስርዓት አገልግሎት እንዲሰጡ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
- በህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶች፣ ማህበራት፣ የሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶችና ተጠቃሚዎች የሚወከሉበት አማካሪ ኮሚቴ ማቋቋም፣ የመካከለኛ ትራንስፖርት መገልገያ መሳሪያዎች የሀገሪቷ የቦታ አቀማመጥ በሚያመች መልኩ እንዲስፋፋ ማበረታታት፣
- ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ የሆኑ ከተሞችን የትራንስፖርት አገልግሎቱ እንዲስፋፋ ማድረግ፣ የአውቶቢስና ታክሲ ፌርማታዎች፣ መናህሪያዎችና መድረሻዎች እንዲሰሩ ማድረግና ማስተዳደር ናቸው፡፡

# የክትትል ኦዲቱ (Follow up audit) ዓላማ

5. የኦዲት ውጤት ክትትሉ ዓላማ በኢትዮጵያ ትራንስፖርት ባለሥልጣን የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ 2005/2006 ዓ.ም በህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር ላይ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት ለባለሥልጣኑ መ/ቤት በላከው ሪፖርት በተገኙ ግኝቶች ላይ በተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች ፤ እንዲሁም ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተሰጡትን ማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ በቁጥር 130/ሕ/ት/ል/ 03/06 ቀን 7/8/2006 በላከው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት ችግሮቹ የተቀረፉ መሆናቸውን መገምገም ሲሆን በክትትል ኦዲቱ ወቅት ያልተቃለሉ/ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ችግሮቹ ያልተቀረፉበትን ምክንያት በመገምገም ለሚመለከተው አካል ለማሳወቅ ነው፡፡

# የክትትል ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

6. የክትትል ኦዲቱ የሸፈነው በትራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤት በህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር ላይ ከ 2002 እስከ 2005 በጀት ዓመት እና በ

2006 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የተከናወነውን የሥራ እንቅስቃሴ መሰረት ባደረገ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ በተሰጡ የማሻሻያ ኃሳቦችን መሰረት አድርጎ መ/ቤቱ ባዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብርን መሰረት  የተከናወኑ ተግባራት ላይ ነው፡፡

7. የክትትል ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በትራንስፖርት ባለሥልጣን ዋና መስሪያ ቤት እና በባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና የድሬዳዋ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤትን በተመለከተ ለትራንስፖርት ባለስልጣኑ ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ማስረጃዎችን በመከለስ ነው፡፡ እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል በክልሉ የትራንስፖርት ኤጀንሲ እና በአዳማ ትራንስፖርት ኤጀንሲ በመገኘት መረጃዎችን በመከለስና ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና እንዲሁም የመስክ ጉብኝት በማድረግ አሰራሩን በመመልከት ነው፡፡

## ለክትትል ኦዲቱ የተለየው አካባቢ/ Follow up Audit Identified Area/

8. ለክትትል ኦዲቱ የተለየው አካባቢ የትራንስፖርት ባለሥልጣን "የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር" በሚል ርዕስ የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት  በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት አድርጎ በባለስልጣን መ/ቤቱ የተዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር ተግባራዊ መደረጉን  መገምገም የሚል ነው፡፡

## የክትትል ኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫና መመዘኛ መስፈርቶች

9. የክትትል ኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫና መመዘኛ መስፈርቶች የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በትራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤት በህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር ላይ የክዋኔ ኦዲት አከናውኖ ለባለስልጣን መ/ቤቱ   ታህሳስ/2006 ዓ.ም በተሰጠ ሪፖርት ላይ የተገለፁትን የማሻሻያ ሀሳቦች ና በመ/ቤቱ የተዘጋጁ የድርጊት መርሃ ግብሮችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡የማሻሻያ ሀሳቡ በአባሪ 1 ላይ ተመልክቷል፡፡

# <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>በክትትል ኦዲቱ (Follow up audit) የተገኙ ግኝቶች</u>

ባለስልጣን መቤቱ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን በቅንጅት መስራቱን በተመለከተ

10. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙ ግኝቶች፤
    - የአዲስ አበባ አነስተኛና መለስተኛ (አዲስ ከተማ) እና የቃሊቲ ጊዜያዊ መናኸሪያዎች ውስጥ ተመሳሳይ ሞዴል ያላቸው አነስተኛና መለስተኛ ተሽከርካሪዎች እንዲጭኑ ከተፈቀደላቸው የወንበር ቁጥር በላይ ተጨማሪ መቀመጫዎች የጨመሩ፣ በወንበሮች መካከል ያለው ርቀት ባለሥልጣኑ ካስቀመጠው የርቀት መጠን ያነሰ ሆኖ የተሰሩ በመኖራቸው ተጠቃሚው ሕብረተሰብ ደህንነቱንና ምቾቱ ሳይጠበቅ የሚጓዝበት ሁኔታ መኖሩን፤
    - በአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ሚኒባስ ታክሲዎችና ድጋፍ ሰጪ ሚኒባሶች በወንበሮች መካከል ያለው ርቀት በደረጃው ከተቀመጠው ያነሰ ሆኖ የተሰሩ መኖራቸው፣ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና የስምሪት አፈፃፀም መመሪያን እንደሚጥስ ሆኖ ተገኝቷል የሚል ነው፡፡
11. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከታዩ የባለስልጣኑ የአዲስ አበባ አዲስ ከተማ አገር አቋራጭና መለስተኛ መናህሪያዎች፣ በላምበረት መናህሪያ፣ በአስኮና በቃሊቲ መናህሪያዎች እንዲሁም በአዳማ መናህሪያ ተመሳሳይ ሞዴል ያላቸው አገር አቋራጭ፣ መለስተኛና አነስተኛ ተሽከርካሪዎች ከተፈቀደላቸው የወንበር ቁጥር በላይ ተጨማሪ መቀመጫዎች ያላስቀመጡ ሲሆን በወንበሮችም መካከል ያለው የርቀት መጠንም የተጓዡን ምቾት ከመጠበቅ አንፃር በ 2005 ዓ.ም የወጣውን የትራንስፖርት መመሪያ መሰርት ያደረገ መሆኑ በመስክ ጉብኝት ታይቷል፡፡
12. ይሁን እንጂ በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት ከተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ ተግባራዊ ያልተደረገው በአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ሚኒባስ ታክሲዎችና ድጋፍ ሰጪ ሚኒባሶች ላይ ትርፍ መቀመጫዎችን የሚያስቀምጡ እና በተሽከርካሪ ውስጥ ካለው የመቀመጫ አቅም በላይ የሚጭኑ መኖራቸው በአካል ምልከታ የታየ ሲሆን ይህም የህዝብ

ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና የስምሪት አፈፃፀም መመሪያን የጣሰ መሆኑ በክትትል ኦዲቱ ታውቋል፡፡

13. ይህን በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸው በአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ የትራንስፖርት ኦፕሬሽን የሥራ ሂደት መሪ በኦዲት ቡድኑ በቃለ መጠይቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ የአጫጫን ስርዓትን ለማስከበር ሲባል የተወሰደ እርምጃ የሌለ መሆኑን፣ ሆኖም በታክሲ ዞናዊ ስምሪቱ አቀራርጠው የሚጭኑ፣ ከታሪፍ በላይ የሚያስከፍሉ፣ በሥራ መውጫና መግቢያ ሰዓት የሚደበቁ ታክሲዎች መኖራቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት ከጥቅምት 20/2007 ዓ.ም ጀምሮ በፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን፣ ከአዲስ አበባ መንገዶች፣ ትራፊክ ፖሊስና ከደንብ ማስከበር፣ ከአንበሳ አውቶቢስ፣ ከፐብሊክ ሰርቪስ እና ከትራንስፖርት ቢሮው በተውጣጣ ስቲሪንግ ኮሚቴ የተሸከርካሪ አቅርቦትን የመጨመርና የከተማውን የትራፊክ ፍሰት ማሳለጥ ዓላማው ያደረገ የአጭር ግዜ መፍትሄ በአዲስ አበባ የታክሲ አገልግሎት በሚያስፈልጋቸው በተለዩ 43 መስመሮች ላይ የድጋፍ ሰጪ ተሸከርካሪዎች በየቀኑ 230 መለስተኛና ከፍተኛ ተሸከርካሪዎችን አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ እየተሰራ ያለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የባለስልጣኑ መ/ቤት ኃላፊዎች ይህን ቢሉም ችግሩ አሁንም ያልተቀረፈ ችግሩን ለመቅረፍ በሚያስችል መጠን ጥረቱ ያልቀጠለ በመሆኑ የተደረገው ድጋፍ በቂ ነው ብሎ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

14. በመሆኑም በአዲስ አበባ የከተማ ታክሲ አገልግሎት የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና የስምሪት አፈፃፀም መመሪያን መሰረት በማድረግ የተገልጋዩን ህዝብ ችግር አለመቅረፍ፣ ከሚገባው መጠን በላይ በመጫን ተገልጋዩን እያንገላቱና ተገቢ ያልሆነ ጥቅም በማግኘት ላይ ይገኛሉ፡፡

**ለህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውል መናህሪያ ቦታ መረጣና ግንባታ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሆኑን በተመለከተ**

15. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙት

- በትራንስፖርት ባለስልጣን ሥር የሚገኘው የድሬዳዋ መናኸሪያ ለጎርፍ ተጋላጭ በመሆኑ መናኸሪያው በክረምት ወራት ኃይለኛ ዝናብና ጎርፍ ሲኖር አገልግሎት መስጠት ስለሚያቆም ሳቢያን በተባለው አካባቢ አዲስ መናኸሪያ ለመገንባት ለእምነቱ እንደሻው የሥራ ተቋራጭ በብር 37, 804,687.00፣ ለአልቲሜት ፕላን ፒ.ኤል.ሲ. አማካሪ አርክቴክት መሐንዲስ አማካሪ ድርጅት በብር 624,312.00 በድምሩ ብር 38,428,999.00 በመቅጠር ሥራ ማስጀመሩ፣ ተቋራጭ ድርጅቱ በውሉ መሰረት መጋቢት 16 ቀን 2004 ዓ.ም

ግንባታውን ጀምሮ በ18 ወራት ውስጥ አጠናቆ መስከረም 16 ቀን 2006 ዓ.ም እንደሚያስረክብ በውሉ ላይ ተቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት ለሥራ ተቋራጩ ቅድሚያ ክፍያ ብር 13,042,617.01 እና ለተሰሩ ሥራዎች ክፍያ ብር 2,603,670.12 በድምሩ ብር 15,646,287.12 የተከፈለና ለአማካሪ መሐንዲሱ በየወሩ ብር 34,684 ሂሳብ በኦዲቱ ወቅት የመስክ ጉብኝት እስከተደረገበት ሐምሌ 2005 ድረስ እየተከፈለ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት ለቢሮ አገልግሎት የሚሆነው ሕንፃ ግንባታ ከመጀመሩ በስተቀር የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚሰጡበት የማቆሚያሥፍራ ግንባታ ሥራ አለመጀመሩ፤

- በአዲስ አበባ ከተማ በምስራቅ መውጫ በር ላምበረት አካባቢ እና በምዕራብ መውጫ በር የአየር ጤና መናኸሪያዎቸ ግንባታቸው በ1995/96 በጀት ዓመት ቢጠናቀቀም ኦዲቱ እሰከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ስራ ያልጀመሩ መሆኑ፣
- የአየር ጤና መናኸሪያ ወደ መናኸሪያው ለመግባትም ሆነ ለመውጣት ከዋናው መንገድ የሚገነጠለው አስፋልት ጠባብ በመሆኑ ለህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለሚሰጡ ተሸከርካሪዎችም ሆነ ተሣፋሪዎችን ለሚያመላልሱ የከተማ የትራንስፖርት አገልግሎት ለሚሰጡ የከተማ አውቶብስና ታክሲዎች ማቆሚያና ማራገፊያ ቦታዎች ያለመኖሩ፤
- የሻሸመኔ እና የቃሊቲ ጊዜያዊ መናኸሪያዎች ግቢያቸው አስፋልት ያልተነጠፈና አሸዋ የፈሰሰበት ሲሆን በተለይ የቃሊት መናኸሪያ አሸዋው በአፈር የተዋጠ ወጣ ገባ በመሆኑ ለተሸከርካሪዎች ተዘጋጅቶ የነበረው ለመኪና ማቆሚያ የተሰራው ፉካ በአፈር የተዋጠ መሆኑ፤
- የአዲስ አበባው የአገር አቋራጭ እና የአዲስ ከተማ አነስተኛና መካከለኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አውቶብስ መናኸሪያዎቹ በ1969 ዓ.ም የተገነቡ በመሆኑ ባለሥልጣኑ ያወጣውን መስፈርት የማያሟሉ መሆኑን እና የአዲስ አበባው የአገር አቋራጭ የሕዝብ ትራንስፖርት አውቶብስ መናኸሪያ ከተሰራ ጀምሮ ጥገና ተደርጎለት የማያውቅ መሆኑ፤ ናቸው፡፡

16. በክትትል ኦዲቱ የድሬዳዋ መናህሪያ ፕሮጀክቱ በተመለከተ የማሻከር ሥራ የሚሰራው አልትሜት ፕላን ድርጅት የድሬዳዋ መናህሪያ ግንባታ 11 ወራትን ዘግይቶ መጠናቀቁን እና ርክክብ መፈፀሙን ለመረዳት ተችሏል፡፡
17. በአዲስ አበባ ከተማ በምዕራብ መውጫ በር የአየር ጤና መናህሪያ ሥራ ያልጀመረ መሆኑ፤ እንዲሁም በክትትል ኦዲት ወቅት በአካል የተጎበኘው የቃሊቲ ጊዜያዊ መናህሪያ ለተሽከርካሪ መንገድ አሸዋ የፈሰሰበት ቢሆንም አሸዋው በአፈር በመዋጡ ለተሽከርካሪ ማቆሚያ ሥፍራነት የማይመች መሆኑን፤
18. የአዲስ አበባ አዲስ ከተማ አገር አቋራጭና መካከለኛና አነስተኛ መናህሪያዎች የባለስልጣኑ መ/ቤት ያወጣውን መስፈርት የማያሚሉ መሆኑ፤ ለመመልከት ተችሏል፡፡
19. በክትትል ኦዲቱ ወቅት ጉዳዩ የሚመለከታቸው የአዲስ አበባ አገር አቋራጭና የአዲስ ከተማ መካከለኛና አነስተኛ የህዝብ ትራንስፖርት አውቶቢስ የመናህሪያ የቡድን መሪዎች በክትትል ኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ መናህሪያዎቹ ለረዥም ግዜ ለ 40 ዓመታት ያህል አገልግሎት የሰጡ በመሆናቸው የተሻሻለ የመናህሪያ ባለቤትነት ና ግንባታ አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያ የካቲት 2003 ዓ.ም ላይ በመናህሪያ ደረጃ መሟላት የሚገባቸውን ያላሟሉ በመሆናቸውና በአሁኑ ወቅትም በባቡር ግንባታ ምክንያት እየፈረሱ በመሆናቸው የነበራቸውን የቦታ ስፋት መጠን ማጣት ችግር ያለ ቢሆም ባለው ደረጃ መሰረት በማሻሻል መነህሪያዎቹ አገልግሎት እንዲሰጡ ጥረት የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
20. የአየር ጤና መናህሪያን በተመለከተ በባለስልጣኑ መ/ቤት የህዝብ ትራንስፖርት አገልግ ሎት ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በክትትል ኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ መናህሪያውን ሥራ ከማስጀመር አንፃር ኮሚቴ ተቋቁሞ ሥራ የሚጀምርበትን ሁኔታ ከአዲስ አበባ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ እና ከልደታና ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ትራንስፖርት ጽ/ቤት ኃላፊዎች ጋር ውይይት የተደረገ መሆኑና በተጨማሪም ከመናህሪያው መውጫና መግቢያ በሮች የመንገድ ግንባታውን አፈፃፀም የገመገሙና በዚህም መሰረት አብዛኛው የግንባታ ተግባር እየተጠናቀቀ በመሆኑ ሥራ ለማስጀመር ክትትል እተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የቃሊቲ መናህሪያን በተመለከተ የህዝብ ትራንስፖርት ስምሪት መናህሪያ አስተዳደር ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ መናህሪያው ስታንዳርድ ባሟላ መልኩ አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑን አስረድተው ግንባታ ለማከናወን የቦታ ርክክብ ጉዳይ ክትትል እየተደረገ የሚገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
21. የሥራ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ችግሮቹ ካለፉት አመታት ጀምሮ እስከ ክትትል ኦዲቱ ማጠናቀቂያ ድረስ ያልተቀረፉ መሆናቸው እንዲሁም ጊዜያዊና ዘላቂ መፍትሄዎችን

በማስቀመጥ ችግሮቹን ለመቅረፍ ያልተንቀሳቀሱ በመሆኑ ኃላፊው የሰጡት መልስ ችግሮቹን ለመፍታት በቂ ናቸው ብሎ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

22. ቀደም ብለው የተሰሩት የአዲስ አበባ አገር አቋራጭና አዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ መናህሪያዎች ወቅታዊ ደረጃዎችን ያልጠበቁ መሆኑ፣ አዲስ ከተሰሩ የአየር ጤና መናህሪያ አገልግሎት እንዲሰጥ አለመደረጉ፤እንዲሁም በቅርቡ ሥራ ጀምሮ አገልግሎት እየሰጠ ያለው የቃሊቲ መናህሪያ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ተገንብቶ የተሟላ አገልግሎት መስጠት አለመቻሉ እና የድሬዳዋ መናህሪያ በታቀደለት ወቅት አለመጠናቀቁ ህብረተሰቡ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ፤ እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ መሰረታዊ የሆኑ መገልገያዎችን ያሟላ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዳያገኝ ያደርጋል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሰረት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ መሰረታዊ የመናህሪያ አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ**

23. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኙት፣
- የአዲስ አበባ የአገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የአስኮ የቃሊቲ እና የድሬዳዋ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሀዋሳ ከተማ፣ በኦሮሚያ ክልል የአዳማ እና ሻሸመኔ ከተማ መናኸሪያዎች ግቢ ውስጥ የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ የሌላቸው መሆኑን፣
- በአዲስ አበባ ከተማ የአዲስ አበባ የአገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የቃሊቲ፣ የአስኮ እና የድሬዳዋ ከተማ፣ የሐዋሳ፣ የሻሸመኔ እና የአዳማ መናኸሪያዎች ለጠፉ ንብረቶች ማቆያ ቦታ የሌለ፣ የተሟላ የመፀዳጃ ቤቶች የሌላቸው መሆኑን፣
- የድሬዳዋ፣ የሐዋሳ እና የአዳማ መናኸሪያዎች የመንገደኞች ማረፊያና መጠበቂያ መጠለያ ቦታ ቢኖራቸውም መቀመጫ ወንበር የሌላቸው መሆኑን፣ የአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የአስኮ፣ የቃሊቲ ጊዜያዊ መናኸሪያዎች እና የሻሸመኔ መናኸሪያ ለተገልጋዮች የመጠለያ ቦታ የሌላቸው መሆኑ፣ የሚሉ ናቸው፡፡

24. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በታዩት የአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ መናሃሪያዎች ማለትም የአስኮ፣ የላም በረት፣ የቃሊቲ እና የአዳማ መናሀሪያዎች እንደሚከተለው ተመልክተዋል፡፡

- በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ በአዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ መናሀሪያዎች በአስኮ፣ ላም በረት እና ቃሊቲ መናሀሪያዎች ግቢ ውስጥ የምርመራ ግዜያቸው በ 3 ዓመት ያለፈባቸው የእሳት አደጋ መከላከያዎች የተገኙ ሲሆን፣ በአዳማ መናሀሪያ የእሳት አደጋ መከላከያው የሌለ(ያልተቀመጠ) መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ከተማ የአዲስ አበባ አገር አቋራጭ መናሀሪያ፣ የአዲስ አበባ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ መናሀሪያዎች ፣ የቃሊቲ፣ የአስኮና የአዳማ መናሀሪያዎች ለጠፉ ንብረቶች ማቆያ በግልፅ ቦታ የሚታይ ማስቀመጫ/ማቆያ የሌላቸው/ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤ እንዲሁም ደረጃቸውን የጠበቁ መፀዳጃ ቤቶች በተለይም የአካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ አለመሆናቸው፤
- የአዳማ ከተማ መናሀሪያ የመንገደኞች ማረፌያና መጠበቂያ መጠለያ ቢኖረውም መቀመጫዎች ያልተዘጋጀለት መሆኑ፣ በአዲስ አበባ ከተማ የአዲስ አበባ አገር አቋራጭ የአዲስ አበባ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ እና አስኮ መናሀሪያዎች የመጠለያ ቦታ ሆነ መቀመጫዎች የሌላቸው መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ አገር አቋራጭና የአዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ፣በላም በረት፣አስኮ፣ ቃሊቲ እና አዳማ መናሀሪያዎች ተሳፋሪዎች ወደ መናሀሪያ ውስጥ ሲገቡ ስለ አገልግሎት አሰጣጡ መረጃ የሚያገኙበት በላም በረት መናሀሪያ ብቻ ኤሌክትሮኒክስ ቢል ቦርድ ያለ ሲሆን በሌሎች መናሀሪያዎች የሌለ መሆኑ፤
- እንዲሁም በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ መናሀሪያ ብቻ ለአቅመ ደካሞችና ለአካል ጉዳተኞች የተለየ የመግቢያ በር የተዘጋጀ ሲሆን፤ በሌሎቹ መናሀሪያዎች አለመዘጋጀቱ፤ ሸኚ በማይገባባቸው የመናሀሪያ በሮች ደንበኞች እቃዎቻቸውን ሊገፉባቸው የሚችሉበት ጋሪዎችን በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ መናሀሪያ መግቢያ በሩ እና ጋሪዎች ያሉ ሲሆን፤ በላም በረት የተለየ መግቢያ በር የሌለ ቢሆንም ጋሪዎቹ ያሉ መሆኑ፤ በአስኮ፣በቃሊቲ እና በአዳማ መናሀሪያዎች የዕቃ መግፊያ ጋሪዎች የሌሉ መሆኑ፤
- በተጨማሪም በአስኮ ለቢሮዎች አገልግሎት ከሚሰጥ መብራት ውጪ ለግቢው አገልግሎት የሚሰጥ መብራት የሌለ መሆኑ፤ በሁሉም በታዩት መናሀሪያዎች ለተሳፋሪው ለመጠጥ አገልግሎት የሚውል ውሃ የሌለ ሲሆን፣ ለአካል ጉዳተኞች መንቀሳቀሻ የሚሆን የተዘጋጀ ዊል ቸር ከቃሊቲና ከአዳማ መናሀሪያ በስተቀር በሌሎቹ የተዘጋጀ መሆኑ ታይቷል፡፡

25. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ መጠይቅ የመናህሪያዎቹ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ በአዲስ አበባ አገር አቋራጭና አዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ መናህሪያዎች ያሉዋቸው የእሳት አደጋ መከላከያዎች የምርመራ ግዜአቸው 3 ዓመት ያለፋቸው ስለመሆኑ የተሰጠው አስተያት ተገቢ መሆኑን አምነው በቀጣዩ ግዜ ሙያተኛ በማሰልጠን የሚያስተካክሉ መሆኑን፤ መፀዳጃዎችን በተመለከተም አገልግሎት መስጠት ከጀመሩ 40 ዓመታት ያለፋቸው በመሆኑ ይዞታቸው የቀነሰ መሆኑን በማመን በ 2008 ዓ.ም አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ በማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ የሚስተካከል መሆኑን፣ የአስኮ መናህሪያ ኃላፊ በእሳት አደጋ መከላከያው ላይ የተሰጠው አስተያየት የሚስተካከል መሆኑን ገልፀው የመፀዳጃ ቤቶችን በተመለከተ የውሃ ችግር ያለበትና የአካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያላደረገ በመሆኑ በ 2008 ዓ.ም የሚያስተካክሉ መሆኑን፣ የቃሊቲ መናህሪያ ኃላፊ የእሳት አደጋ መከላከያውን አስተያት የሚያስተካክሉ መሆኑን ገልፀው የመፀዳጃ ቤትን ችግር በተመለከተ የችግሩ መንስኤ ደረጃውን የጠበቀ የመናህሪያ ግንባታ አለመሰራቱ መሆኑን ሲገልፁ፣ በአዳማ መናህሪያ ችግሩ መኖሩን አምነው የችግሩ መንስኤ የበጀት ችግር ምክንያት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

26. ስለ ሁኔታዎቹ የአገር አቋራጭ አውቶቢስ ተራ መናህሪያ የቡድን መሪ በሰጡት መልስ ለተሳፋሪው ኢንፎርሜሽን ማስተላለፍን በተመለከተ በድምፅ ማጉያ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ፤ በቢል ቦርድ ለማቅረብ ተሞክሮ ጥቂት ቀናት ስርቶ በብልሽት ምክንያት የተቋረጠ መሆኑን አስረድተው በ 2008 ዓ.ም በትራንስፖርት ባለስልጣን የ አይቲ ባለሙያዎች አስጠግኖ ሥራ ለማስጀመር መታሰቡን የገለፁ ሲሆን፤የአዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ መናህሪያ ጊዜያዊ የቡድን መሪ በሰጡት መልስ በባቡር ግንባታ ምክንያት በተደጋጋሚ አጥሩ በመፍረሰሱ ኤሌክትሮኒክስ ቢል ቦርድ እና ኢንፎርሜሽን ዴስክ በተለይም አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ በመግቢያ በሮች አካባቢ አለመኖሩን፤ ሆኖም ግን በ 2008 ዓ.ም ተግባራዊ የሚያደርጉ መሆኑን፤እንዲሁም የአካል ጉዳተኛና የአቅመ ደካማ መውጫና መግቢያ በሮች፣ ሸኚ የማገባባቸው በሮች በጋሪ ዕቃዎችን ለማስገባት የሚያገለግሉ እና የሚዛን አገልግሎት እንዲኖር በ 2008 ዓ.ም ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩ መሆኑን የገለፁ ሲሆን የቃሊቲ መናህሪያ ቡድን መሪ ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክስ ቢል ቦርድ ወይም ኢንፎርሜሽን ዴስክ በተለይም የአካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ አለመኖር በእቅድ ተይዞ ያለመሰራቱ ጉዳይ ሲሆን የተለዩ የመግቢያ በሮች አለመዘጋጀት ዋናው ምክንያት ደረጃውን የጠበቀ የመናህሪያ ግንባታ ባለመገንባቱ መሆኑን ሲገልፁ የአዳማ መናህሪያን በተመለከተ የስምሪትና ክትትል ፈፃሚ ችግሩ መናህሪያው ቀድሞ የተሰራ በመሆኑና የጥገና ግንባታም ለማካሄድ የበጀት ችግር በመኖሩ መሆኑን አመልክተው ፤ዘመናዊ መናህሪያ ግንባታ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን አዲስ የሚገነባ

መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የአዳማ ከተማ መናህሪያን አስመልክቶ የኦሮሚያ ክልል ትራንስፖርት ኤጀንሲ ምክትል ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ መናህሪያው ቀደም ሲል ፌዴራል ያስገነባው በመሆኑ ችግሩ ያለ መሆኑን ገልፀው በ 2008 በጀት ዓ.ም በጀት ከተፈቀደ ችግሩ የሚፈታ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

27. የሥራ ኃላፊዎቹ ከላይ የተገለፁትን ምክንያቶችን የገለፁ ቢሆንም ችግሮቹን ለማስተካከል የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅተው የነበረ በመሆኑ ለምን እንዳልተተገበረ መልስ ያልሰጡ በመሆኑ እንዲሁም በጀት አለመፈቀዱን አስመልክቶ የበጀት ጥያቄ አቅርበው ያልተፈቀደላቸው መሆኑን ማስረጃ ማቅረብ ባለመቻላቸው የሰጡትን መልስ መቀበል አዳጋች ይሆናል፡፡

28. በመሆኑም የህዝብ ትራንስፖርት መሰረታዊ አገልግሎት መሟላት ላይ በመናህሪዎች ውስጥ ደረጃውን ያሟላ የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ አለመቀመጥ፣ የጠፉ ንብረቶች በግልፅ በሚታዩ ቦታዎች አለመኖር እና ለተሳፋሪዎች በተለይም ለአካል ጉዳተኞችና ለአቅመ ደካሞች የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎች አለመሟላታቸው ለእንግልትና አላስፈላጊ ወጪዎ እንዲዳረጉ ያደርጋል፡፡

**የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች በተሰጣቸው ስምሪትና ታሪፍ መሰረት አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑን በተመለከተ**

29. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙ ግኝቶች፡

- በኦዲቱ ወቅት በታዩት በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የአስኮ፣ የቃሊቲ ጊዜያዊ፣ የድሬዳዋ፣ የሀዋሳ፣ የአዳማ እና የሻሸመኔ ከተማ መናኸሪያዎች ስምሪት የሚወስዱ የህዝብ ማመላለሻ ተሸከርካሪዎች መናኸሪያ ውስጥ እያሉ የሚሄዱበትን መስመር እና የሚከፈለውን ዋጋ ታሪፍ አብዛኞቹ በውጭ በኩል ብቻ የሚለጥፉ ሲሆን ከመናኸሪያ ሲወጡ ግን በተለይ ሚኒባሶቹ የለጠፉትን ዋጋ አንስተው የሚንቀሳቀሱ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ከተማ፣ በሐዋሳ እና በሻሸመኔ የከተማ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ታክሲዎች የሚሄዱበትን መስመር የሚሳይ ሰሌዳ (ታፔላ) ተሰርቶላቸው የሚለጥፉ ቢሆንም ለርቀቱ የሚያስከፍሉትን ዋጋ የማይለጥፉ መሆኑን፣
- በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለድጋፍ ሰጪነት በተጨማሪ የተመደቡት ኮድ 3

ሚኒባሶች የተመደቡበትን መስመርና የሚስከፍሉትን ዋጋ አብዛኛዎቹ የማይለጥፉ መሆኑን፣

- ለህዝብ ማማላለሻ ፈቃድ ያልተሰጣቸው ደረጃ የሌላቸውና ለሌላ ንግድ ሥራ ኮድ 3 ሰሌዳ የወሰዱ ሚኒባሶች ጭምር የታክሲ አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑ፤
- የባለሥልጣኑ የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የስምሪት መስመሮችን ርቀት እና የሚከፈለውን ዋጋ የሚያሳይ ሰሌዳ በከተማው የተለያየ ቦታ አሰርቶ ተክሎ የነበረ ቢሆንም ሰሌዳዎቹ ባልታወቀ ምክንያት መነሳታቸው፤
- ከዚህ በተጨማሪ የአዲስ አበባ ከተማ የታክሲ ዞኒንግ ስምሪቱን በአግባቡ እንዲመሩ ኃላፊነት የተጣለባችው የታክሲ ባለንብረት ማህበራት ቢሆኑም ከሥርዓቱ ውጭ በሚሰሩና እየቆራረጡ በሚጭኑ፣ ከታሪፍ በላይ በሚያስከፍሉ፣ ወደ ስምሪት ስርዓቱ በማይገቡ ታክሲዎች ላይ እርምጃ የማይወስዱ መሆኑን፣ በስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት የታክሲዎች በሥራ ላይ አለመሰማራት፣ ከታሪፍ በላይ ማስከፈል፣ መስመር መቆራረጥ ችግሮች መኖሩን፣ በአዲስ አባባ በየተርሚናሉ የተደራጁ ተራ አስከባሪዎች ህግና ደንብ አክብረው አለመስራትና የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች እያቆራረጡ ሲጭኑም ሆነ ከታሪፍ በላይ ሲያስከፍሉ ያለመቆጣጠር፣ ችግሮች መኖራቸው፤ ናቸው፡፡

30. የትራንስፖርት ስምሪትና የአቅጣጫ ስርዓትን ለማሻሻል በ 2005 ዓ.ም /መጋቢት/ በወጣ የታሪፍ ክፍያ መመሪያ መሰረት አሽከርካሪዎች እያስከፈሉ ስለመሆኑ በባለስልጣን መ/ቤቱ በተደረገው የክትትልና ቁጥርር ምርመራ በ 2007 በጀት ዓመት ከታሪፍ በላይ አስከፍለው በተገኙ 187 ተሽከርካሪዎች ላይ የዲስፕሊን እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ከትራንስፖርት ባለስልጣን ከ 2007 ዓ.ም በጀት ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርት መረዳት ተችሏል፡፡
31. በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ የከተማ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ታክሲዎች የሚሄዱበትን መስመር የሚያሳይ ሰሌዳ/ታፔላ/ ተሰርቶላቸው የሚለጥፉ ቢሆንም ለርቀቱ የሚያስከፍሉትን ዋጋ የማይለጥፉ መሆኑን፤እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለድጋፍ ሰጪነት የተመደቡት ኮድ 3 ሚኒባሶች የተመደቡበትን መስመርና የሚያስከፍሉትን ዋጋ አብዛኞቹ የማይለጥፉ ሆነው የተገኙ ሲሆን፣ የባለስልጣን መ/ቤቱ የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የስምሪት መስመሮችን እርቀትና የሚከፈለውን ዋጋ የሚያሳይ ሰሌዳ በከተማው

ውስጥ በተለያየ ቦታ አሰርቶ ተክሎ የነበረ ቢሆንም በኦዲት ውጤት ክትትሉ ወቅት በቦታቸው የሌሉ መሆኑ በአካል እይታ ታውቋል፡፡

32. ስለ ጉዳዩ በአዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ መናህሪያ ግዜያዊ ቡድን መሪ በኦዲት ቡድኑ በቃለ መጠይቅ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ተሽከርካሪዎቹ ከክልሎች ሲነሱ ቁጥጥርና ክትትል የማይደረግባቸው በመሆኑ ሲሆን በአዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ መናህሪያ ውስጥም ቁጥጥር ቢኖርም የጠነከረ አለመሆኑን ሲገልፁ የአስኮ መናህሪያ ቡድን መሪ ችግሩ መኖሩን አምነው የሚያስተካክሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

33. የአዲስ አበባ ከተማ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ ዋና የሥራ ሂደት መሪ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ከጥቅምት 20/2007 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት መገኘት ከነበረባቸው ታክሲዎች መካከል በ 80% በማሳደግ ከ 3500 ወደ 6500 ከፍ እንዲል የተደረገ መሆኑን ገልፀው ለዘህም ድጋፍ የሚሰጡ በየቀኑ በአማካኝ 4200 የሚሆኑ ኮድ 3 ኦሮ፣ አማ፣ ደቡብ ህዝቦችና አዲስ አበባ የሚል ሰሌዳ ያላቸው ሚኒባስና ቅጥቅጥና መለስተኛ አውቶቢሶች የተመደቡ መሆናቸውን ፤ህግና ስርዓት ከማስከበር አንፃር በ 2767 ታክሲና ድጋፍ ሰጪ ተሽከርካሪዎች ላይ የገንዘብ ቅጣት መፈፀሙን ገልፀዋል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከግንቦት 2003 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ለተደረገው የታክሲ ዞናዊ ስምሪት በ 157 ተርሚናሎች የመነሻና መድረሻ ታፔላዎች ተተክለው የነበረ ቢሆንም በቀላል ባቡሩ መንገድ ግንባታ ምክንያት የተነሱ ያሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

34. የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የተሰማሩ ባለንብረቶችና ማህበራት አገልግሎት የሚሰጡበትን መስመርና ታሪፍ በግልፅ በሚታይ ቦታ አለመለጠፋቸው እና የመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ቁጥጥሩን በአግባቡ አለማከናወናቸው ህብረተሰቡን ለአለስፈላጊ ወጪ እንዲዳረግ ያደርጋል፡፡

**ደረጃ የተሰጣቸው የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በሙሉ ለደረጃው የተቀመጠውን ቀለም መቀባታቸውን በተመለከተ**

35. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙ ግኝቶች

- በባለስልጣን መ/ቤቱ በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና ሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ከደረጃ አንድ እሰከ ሦስት ላሉት የተለያየ የመለያ ቀለም አዘጋጅቷል፡፡ መለስተኛ የህዝብ ማመላለሻ አውቶብሶች እና አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች (ሚኒባሶች) ለተሰጣቸው ደረጃ የሚገባውን ቀለም ተቀብተው አልተገኙም፤ የሚል ነው፡፡

36. በክትትል ኦዲቱ በአካል በታዩ መናህሪያዎች በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ በአዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ፣ በላምበረት፣ በአስኮ፣ በቃሊቲ እና በአዳማ መለስተኛ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችና አነስተኛ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ለተሰጣቸው ደረጃ የሚገባውን ቀለም ሳይቀቡ፤ ሆኖም ግን በምትኩ ተመሳሳይ ስቲከር ቀለም ለጥፈው ተገኝተዋል፡፡

37. ስለ ጉዳዩ በፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ስር ያሉ በአዲስ አበባ የአዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ፣ ላም በረት፣ አስኮ እና ቃሊቲ መነሀሪያ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ተመሳሳይ መልስ የተሽከርካሪዎቹ ባለንብረቶች የተደራጁት በክልሎች በመሆኑ ክልሎች በመመሪያው መሰረት እንዲቀቡ ባለማድረጋቸው መሆኑን አመላክተው በእነሱ በኩል ግን በመመሪያው መሰረት በ 2008 ዓ.ም እንዲቀቡ ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

38. በተጨማሪም በመስክ በታየው በአዳማ መናህሪያ ሚኒባስ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በሙሉ ለደረጃቸው የተፈቀደውን ቀለም ሳይቀቡ በተመሳሳይ ቀለም የተዘጋጀ ስቲከር መለጠፋቸውን የአዳማ ትራንስፖርት ኃላፊ የሚያውቁ መሆኑን ገልፀው የችግሩ መንስኤ የተሽከርካሪዎቹ ባለንብረቶች ካቀረቡአቸው ችግሮች ለምሳሌ በተሽከርካሪዎች የደረጃ መውረድ ወቅት እንደገና ለደረጃው የሚያስፈልግ ቀለም ቀቡ በሚባልበት ጊዜ ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርገን የሚችል ነው ከማለታቸው የተነሳ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

39. የሥራ ኃላፊዎቹ ከላይ የተገለፁትን ምክንያቶችን የገለፁ ቢሆንም ችግሮቹን ለማስተካከል የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅተው የነበረ በመሆኑ ለምን እንዳልተተገበረ መልስ ያልሰጡ በመሆኑ እንዲሁም በተሽከርካሪዎች ቀለም አለመቀባት የተሰጠው መልስ ከባለንብረቶቹ የተነሳውን ጥያቄ ለሚመለከተው አካል አቅርበው ውሳኔ ማቅረብ ባለመቻላቸው ችግሮቹን ለመፍታት በቂ ጥረት ያላደረጉ በመሆኑ ምላሹን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

40. መለስተኛና አነስተኛ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ለደረጃቸው የተፈቀደላቸውን ቀለም ቀብተው ያልተገኙ በመሆኑ ተገልጋዩ ህብረተሰብ በቀላሉ ደረጃቸውን እንዳይለዩና ከደረጃው የሚገባውን አገልግሎቶች እንዳያገኙ ከማድረጉም በላይ የህዝብ ማመላለሻ ፈቃድ የሌላቸው ተሽከርካሪዎች በህገ ወጥ መንገድ ስምሪት ላይ እንዲሳተፉ በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን በመመሪያው መሰረት በየደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት አሟልተው መስራታቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ**

41. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኙ ግኝቶች፣

- መናኸሪያዎች ውስጥ በአንዳንድ መለስተኛ እና አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት የሚሰጡ አሽከርካሪዎች እና ረዳቶች በመመሪው መሰረት ለደረጃው የሚገባውን የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) የማይለብሱ መሆኑን፣
- በሁሉም ደረጃ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች አስገዳጅ ናቸው ተብሎ የተቀመጡ ቁሳቁሶችን፣ የመንገደኛ መቀመጫ ወንበር ከፊትና ከኋላው 730 ሚ.ሜ ስፋት፣ ጥራት ያለው ከጥጥ ጨርቆች የተሰራና  በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መጋረጃ፣ የተሽከርካሪው ወለል ሙሉ ለሙሉ "ባለሳንቲም" ኘላስቲክ ያልተሸፈኑ መሆኑ፤
- ከዚህም በተጨማሪ ሥሪታቸው ለሌላ ተግባር የነበሩ ተሽከርካሪዎች ወደ ሕዝብ ማመላለሻነት እንዲቀየሩ ፈቃድ ሲሰጣቸው  ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሕዝብ ማመላለሻ ተሻካርካሪዎች ያወጣውን መስፈርት ሳያሟሉ ለታክሲ እና ከከተማ ውጭ እንዲያገለግሉ ሠሌዳና ደረጃ የሚሰጣቸው መሆኑ፤ ናቸው፡፡

42. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በክዋኔ ኦዲቱ የተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ ተግባራዊ ባለመደረጉ በአካል በታዩ በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ በአዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ፣ በላም በረት፣ በአስኮ፣ በቃሊተና በአዳማ መናህሪያዎች ውስጥ የአገር አቋራጭ፣ የመለስተኛና አነስተኛ የህዝብ ማመላለሻ የሚሰጡ አሽከርካሪዎችና ረዳቶቻቸው በመመሪው መሰረት ለየደረጃው የሚገባውን የደንብ ልብስ አሟልተው የማይለብሱ መሆኑን በአካል ለማየት ተችሏል፡፡
43. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በአካል በታዩት  በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ ተሽከርካሪዎች ውስጥ በመቀመጫ ወንበር ስፋት መጠን፣ ንጣፎች እና የእሳት አደጋ መከላከያዎችን አሟልተው የተገኙ ሲሆን መጋራጃን በተመለከተ በመመሪያው የተቀመጡትን እና በመመሪያው ያልተቀመጡትን ዓይነት መገረጃዎች ንፅህናቸው ባልተጠበቀ ሁኔታ ሲገለገሉ ታይተዋል፡፡
44. በተጨማሪም ስሪታቸው ለሌላ ተግበር የነበሩ ተሽከርሪዎች ወደ ህዝብ ማመላለሻነት እንዲቀየሩ ፈቃድ ሲሰጣቸው ባለስልጣን መ/ቤቱ ለህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ያወጣውን መስፈርት ማሟላታቸውን የሚያረጋግጥ ስለመሆኑ የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ የሥራ ሂደት የአሰራር መመሪያ ቁጥር 2 /ነሐሴ 2006 ዓ.ም/ የተዘጋጀ  ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ከመረጃው መረዳት ተችሏል፡፡

45. ስለጉዳዩ የየመናህሪያ ኃላፊዎች በየደረጃው ያሉ ተሽከርካሪዎች ውስጥ ያሉ መጋረጃዎችን ንፅህና አጠባበቅ በተመለከተ ለቀረበላቸው ቃለ -መጠይቅ በሰጡት ተመሳሳይ መልስ የመጋረጃዎች ንፅህና እንዲጠበቅ በየዕለቱ ቁጥጥር ካለማድረግ መሆኑን የገለፁ ሲሆን የደንብ ልብስ አሟልቶ የመልበስ ሁኔታን በተመለከተ ቁጥጥር ያለ ቢሆንም ሽሚዝ፣ክራቫትና ኬፕ ላይ ትኩረት ባለመሰጠቱ በመሆኑ በ 2008 ዓ.ም  የሚስተካከል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

46. ባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን ብቃታቸውን በመለየት አስገዳጅ ናቸው ተብለው የተቀመጡ መስፈርቶችን ተግባራዊ በማድረግ ደረጃ አለመስጠቱ ህብረተሰቡ ለሚከፍለው ገንዘብ ተመጣጣኝ አገልግሎት እንዳያገኝ ያደርገዋል፡፡

## ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአገር አቀፍ ደረጃ የፍጥነት ወሰን መመሪያ ወቅታዊ በማድረግ መተግበሩን በተመለከተ

47. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኘ ግኝት

- የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ሊሄዱበት የሚገባ የፍጥነት ወሰን የካቲት 15/1961 ዓ.ም በደንብ ቁጥር 361/1961  የወጣ ቢሆንም 45 ዓመት የሆነው በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ እና ወቅታዊ መሻሻል ያልተደረገበት መሆኑ፤የሚል ነው፡፡

48. በክትትል ኦዲቱ መረዳት እንደተቻለው ባለስልጣን መ/ቤቱ በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ  የፍጥነት ወሰንን የካቲት 15/1961 ዓ.ም በደንብ ቁጥር 361/1961 ከ 45 ዓመት  በፊት  የወጣውን በማሻሻል ተግባራዊ አለማድረጉን ነው፡፡

49. ስለ ጉዳዩ የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የህዝብ ትራንስፖርት ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የፍጥነት ወሰንን በተመለከተ ደንቡ ተረቅቆ ለመንግሥት የቀረበ መሆኑን ሲገልፁ የኦሮሚያ ትራንስፖርት ኤጀንሲ ምክትል ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ከክልል ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ደካማ ሲሆን፤ ክልሉ ግን እየደረሰ ላለው የትራፊክ አደጋ ትልቁ ምክንያት ከፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር በመሆኑ ይህን ለመቆጣጠር በተለያዩ ግዜያት በክልሉና ሌሎች ሚዲያዎች ግንዛቤ እየሰጡ መሆናቸውን እና የፍጥነት ወሰን ለመቆጣጠር የሚያስችል ቴክኖሎጂ/ራዳር/ ሥራ ላይ በማዋልም በኩል በአገር አቀፍ ደረጃ ክልሉ በምሳሌነት የሚታይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

50. ባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ሊሄዱበት የሚገባ የፍጥነት ወሰን የሚደነግግ መመሪያ በ 1961 ዓ.ም የወጣ በመሆኑ፣ የቆየና በአሁኑ ሰዓት ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበና ወቅታዊ መሻሻል ያልተደረገበት በመሆኑ የህዝብ ማመላለሻ አሽከርካሪዎች በከፍተኛ ፍጥነት እየተጓዙ ከፍተኛ የሆኑ የህይወት መጥፋትና የንብረት ውድመትን እያስከተለ ይገኛል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ በቀንና በሌሊት የሚፈፀሙ ህገ ወጥ ስምሪትን ለማስቆም የወጡ ደንቦችና የአሰራር መመሪያዎችን ተግባራዊነት የሚከታተል መሆኑን በተመለከተ**

51. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኘ ግኝት

- ባለስልጣን መ/ቤቱ የካቲት 2005 ዓ.ም ሕገ ወጥ ስምሪትንና የሌሊት ጉዞ ለመግታት የሚያስችል አገራዊ የአሰራር ደንቦችና መመሪያዎች አውጥቶ ለቅርንጫፍ መ/ቤቶችና ለክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች ያሰራጨ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት መናኸሪዎያችም ሆነ በናሙና በተመረጡ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የትራንስፖር ቢሮ፣ በኦሮሚያ ክልል ትራንስፖርት ኤጀንሲ፣ ምእራብ አርሲ ዞን ሻሸመኔ ከተማ አስተዳደር ትንስፖርት ኤጀንሲ፣ በአዳማ ትራንስፖርት ጽ/ቤት እና በሐረሪ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት ቢሮዎች እንደታየው የሕገ ወጥ ሥምሪቱ በየመናኸሪያዎች በር ላይ ጭምር በግልፅ የሚከናወን መሆኑ፣ ድርጊቱን ለመከላከል በሁሉም ባለድርሻ አካላት በኩል ወጥ የሆነና ቅንጅታዊ አሰራር የሌለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፤የሚል ነው፡፡

52. ባለስልጣን መ/ቤቱ የመንገድና ትራፊክ አደጋን ለመቀነስ ቅንጅታዊ አሰራር ምትክ አይገኝለትም በሚል ከተዘጋጀ የግንዛቤ ማስጨበጫ ቢ.ጋር/መጋቢት 2007 ዓ.ም አዲስ አበባ/ ማስረጃ ስልጠና መስጠቱ መረዳት የተቻለ ቢሆንም በፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን በቀረበ የመስክ ጥናት ሪፖርት/ሰኔ 2007 ዓ.ም/ ችግሩን ከመግታት አንፃር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይበልጥ ጠንክሮ መሰራት ያለበት መሆኑን፤ እንዲሁም በአጠቃላይ የመስክ ጥናት በተደረገባቸው ክልሎች በመስክ ጥናት ሪፖርቱ ገፅ 38 ተ.ቁ 9 ላይ ህገ ወጥ ስምሪትና የሌሊት ጉዞ ሊቆም አለመቻሉ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

53. በመናህሪዎች መካከል ትስስርን አጠናክሮ መቀጠልን በተመለከተ ከክልሎች ጋር በአገራዊ አፈፃፀም መመሪያ፣ መስመር አጥፊው በሚመለሱ ተሽከርካሪዎች፣ በመናህሪያ አገልግሎት አሰጣጥ፣ በህገ ወጥ ስምሪት፣ በትኬት አቆራረጥና በሌሎች አሰራሮች ላይ በመስክ ምልከታ

ጥናትና በደብዳቤ ግንኙነት በማድረግ የድጋፍ ክትትል መደረጉ በ2007 ዓ.ም በጀት ዓመት አፈፃፀም ሪፖርት ላይ የተገለፀ ቢሆንም ችግሩ መፈታት ያልቻለ መሆኑ ታይቷል፡፡

54. ስለ ጉዳዩ የኦሮሚያ ትራንስፖርት ኤጀንሲ ምክትል ኃላፊ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ህገ ወጥ ስምሪትን በክልሉ ለመግታት ከሌሎች አጎራባች ክልሎች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ፈጥረው እየሰሩና ጥረት እያደረጉ ቢሆንም ህገወጦች እያደረጉት ካሉት እንቅስቃሴ አንፃር የትራፊክ መቆጣጠሪያ ኬላ መመስረት እንዳለበት የታመነ ቢሆንም ኬላ እንደ አጠቃላይ እንዲነሳ በመደረጉና ሌሊት የሚቆጣጠር አካል አለመኖሩ ሥራውን አዳጋች ማድረጉን ሲገልፁ፤የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣኑ መ/ቤት የህዝብ ትራንስፖርት ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ አፈፃፀሙ በሁሉም ክልሎች ላይ ወጥ ባይሆንም መመሪያውን የመተግበር ሥራ እየሰሩ ለመሆናቸው ከውይይትና ከጥናት ሰነዶች መገንዘብ እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡

55. ባለስልጣን መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር ተቀናጅቶ የቀንም ሆነ የሌሊት ህገ ወጥ ስምሪት ላይ የተጠናከረ የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰዱ የሰዎች ህይወት አደጋ ላይ እንዲወድቅ ያደርጋል፡፡

### ባለሥልጣን መ/ቤቱ  ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን እንዲፈፀሙ በሚተባበሩ አስፈፃሚ ሰራተኞች ላይ የሚያደርገውን ክትትል በተመለከተ

56. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኘ ግኝት

- መጋቢት 2005 ዓ.ም በተሻሻለው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና ሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ መሰረት የተሸከርካሪ የኋላ ሰሌዳ በሚመለከተው አካል ከተፈታ በኋላ ቅጣቱን ሳይፈፅም በያዘው የቅጣት ሰነድ (የቁጥጥር ክስ ወረቀት) መስራት እንደማይፈቀድለት፣ ይህንን ህግ ጥሶ የተገኘ አሽከርካሪ ላይ ብር 4000 ቅጣት እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መሰረዝ እንደሚያደርስ መመሪያው ላይ የተቀመጠ ቢሆንም፣ በመስክ ጉብኝት ወቅት በርካታ ቁጥር ያላቸው ሚኒባሶች የኋላ ታርጋቸው ተነቅሎ የስምሪት ፍቃድ ተሰጥቷቸው ሲንቀሳቀሱ ታይቷል የሚል ነው፡፡

57. በክትትል ኦዲቱ ወቅት በአካል በታዩት በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣በአዲስ አበባ መለስተኛና አነስተኛ፣ በላምበረት፣ በአስኮ፣ በቃሊቲና በአዳማ መናሀሪያዎች ከላይ የተገለፁ ችግሮች ተሽከርካሪዎች ላይ አልታዩም፡፡ ስለጉዳዩ የመናህሪያዎች የቡድን መሪዎች

ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ሰሌዳቸው በሚመለከተው አካል የተፈታባቸው ተሽከርካሪዎች ስምሪት የማይሰጣቸው መሆኑን በተመሳሳይ መልስ ገልፀዋል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓቱ በቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን በተመለከተ**

58. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኘው፤ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የራሱንም ሆነ ከስሩ ያሉ መናኸሪያዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲሁም የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርአት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያልተደገፈ መሆኑን ወቅታዊና አገራዊ የትራንስፖርት መረጃ በተሟላ መልኩ ያልተያዘ መሆኑን፤ ነው፡፡
59. በክትትል ኦዲቱ ወቅት የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓቱን በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት በቴክኖሎጂ ተደግፎ እንዲሰራ ያላደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡
60. የኦሮሚያ ትራንስፖርት ኤጀንሲ ምክትል ኃላፊ ስለጉዳዩ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ በዚህ ዓመት የተሽከርካሪና የአሽከርካሪዎች መረጃዎችን በዳታ ቤዝ ያስገቡና ለፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤትም እየላኩ ያሉ መሆኑን እና የመረጃ ልውውጡ በጥሩ ሁኔታ ላይ ያለ መሆኑን፤ እንዲሁም መረጃ በማቀናጀት ለሚመለከተው አካል የሚሰጥ የአይሲቲ/ICT/ አንድ ዲፓርትመንት በመዋቅር ውስጥ ተካቶ የተጠና መሆኑን እና በቀጣይ ጥራቱ የጠበቀ ሥራ የሚሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
61. የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ የትራንስፖርት ኦፐሬሽን ዋና የሥራ ሂደት መሪ ስለጉዳዩ በሰጡት መልስ ከባለስልጣኑ ጋር ያላቸው የመረጃ ልውውጥ በአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ዳታ ቤዝ በባክ አፕ አፕዴት በማድረግ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፤ ነገር ግን የመረጃ ልውውጡ በተሟላ መልኩ ነው ብሎ ለማለት በማያስደፍር መልኩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
62. ስለ ጉዳዩ የባለስልጣኑ መ/ቤት የህዝብ አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ በቃለ መጠይቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ የትራንስፖርት መረጃ አያያዙና ልውውጥ ስርዓት በማንዋል እየተሰራ ያለ መሆኑን አመልክተው ነገር ግን በ 2008 ዓ.ም በአይቲ/IT/ የተደገፈ ሥራ ለመሥራት በእቅድ የተያዘ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

63. ባለስልጣኑ መ/ቤት የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓቱን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለመተግበር በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት ለተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ የድርጊት መርሃ ግብር የቀረፀ ቢሆንም ለምን እንዳልተተገበረ መልስ ያልሰጠ በመሆኑ በ 2008 ዓ.ም ይተገበራል የሚለውን ለመቀበል አዳጋች ይሆናል፡፡

64. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአገር አቀፍ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና ለውውጥ ስርዓትን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ አለማድረጉ በወቅታዊ መረጃ ላይ የተደገፈ ውሳኔ ለመወሰን አዳጋች ያደርግበታል፡፡

**ባለስልጣን መ/ቤቱ የትራንስፖርት ደንቦች፣ መመሪያዎች፤ስታንዳርዶች፣ የተለያዩ ጥናቶችና የሥራ አቅዶች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ የሰራ መሆኑን በተመለከተ**

65. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኘ ግኝት፤ ባለስልጣን መ/ቤቱ በወጡ የህዝብ ትራንስፖርት ደንቦች መመሪያዎች፣ መለኪያ መስፈርቶች፣ ስታንዳርዶች፣ የተለያዩ ጥናቶች፤ የሥራ እቅዶች የመሳሰሉት ላይ ለክልል ትራንስፖርት ቢሮዎችም ሆነ ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ በተጠናከረና ተከታታይ በሆነ መልኩ የማይሰጥ መሆኑ የሚል ነው፡፡

66. ባለስልጣን መ/ቤቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ የሰራ ስለመሆኑ በክትትል ኦዲት ወቅት ከታዩ ከሚከተሉት ማስረጃዎች ማለትም፡-

- በህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ የታዩ ችግሮችና መከናወን የሚገባቸው ተግባራት ውይይት የተደረገበት /ነሀሴ 2006 ዓ.ም አዲስ አበባ /፣
- ለአሽከርካሪዎችና ኦፕሬተሮች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተሰጠ የግንዛቤ ማስጨበጫ/የካቲት 2007 ዓ.ም አዲስ አበባ/፣
- የመንገድ ትራፊክ አደጋን ለመቀነስ ቅንጅታዊ አሰራር ምትክ አይገኝለትም የግንዛቤ ማስጨበጫ ቢጋር /መጋቢት 2007 ዓ.ም አዲስ አበባ/፣
- በህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የደንበኞች እርካታ ደረጃ ለማወቅ የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት/ ሰኔ 2006 ዓ.ም እና ግንቦት 2007 ዓ.ም አዲስ አበባ/፣
- የመስክ ጥናት ሪፖርት /ሰኔ 2007 ዓ.ም/ እና ከክልል ትራንስፖርት ቢሮዎችና ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት መሥሪያ ቤቶች ጋር ትራንስፖርት ባለስልጣን ያደረገው ሀገራዊ ምክክር ቃለ ጉባኤ /የካቲት 19- 20/2007 ዓ.ም/፣
- የትራንስፖርት ባለስልጣን የሰኔ 2007 ዓ.ም እና የ 2007 ዓ.ም በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም በሚል ከተዘጋጁ ማስረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡

67. ስለ ጉዳዩ በስፋት ለማጥራት የትራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የትራንስፖርት ባለስልጣንና የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች አገራዊ የምክክር ጉባኤ መድረክ ላይ መመሪያና ደንቦችን ባለመረዳት የታዩ ችግሮችና ክፍተቶች በማንሳት ዝርዝር የአፈፃፀም የድርጊት መርሀ-ግብር በማዘጋጀት ወደ ተግባር ለመግባት ከክልሎች ጋር መግባባት ላይ መደረሱን እና በመስክ እይታ ወቅት ክፍተት በታየባቸው ክልሎች ላይ በቀረቡት መስፈርቶች፣ ስታንዳርዶችና የመመሪያ ክፍተቶች ማብራሪያ የተሰጠ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

68. የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ የትራንስፖርት ኦፕሬሽን ዋና የሥራ ሂደት መሪ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎችን ለባለድርሻ አካላት በማስገንዘብ ዙሪያ ባለስልጣኑ መ/ቤት በራሱ ጊዜ የሚፈፅመው ተግበር መሆኑን አስገንዝበው በቢሮው በኩል ግን ከከተማ ትራንስፖርት ጋር በተያያዘ የወጡ የአሰራር መመሪያዎችን ከማስፈፀም አንፃር በባለድርሻ አካላት ላይ የሚታይ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት የማስተካከያ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ የተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

69. የኦሮሚያ ትራንስፖርት ኤጀንሲ ቢሮ ኃላፊ ስለ ጉዳዩ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በአገር አቀፍም ሆነ በክልል በአሰራር መመሪያዎች ላይ ለትራንስፖርት ማህበራት በተለያዩ ሚዲያዎች ህብረተሰቡ እንዲያውቅ መደረጉን፣ በተጨማሪም በየዓመቱ በመመሪያዎች አተገባበር ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በመለየት በዓመታዊ እቅድ ላይ በማካተት በተለይም በመጀመሪያ እሩብ ዓመት ላይ በሚዘጋጁ መድረኮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እየተሰራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

70. ባለስልጣን መ/ቤቱ የትራንስፖርት ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ስታንዳርዶች፣ የተለያዩ ጥናቶችና የሥራ አቅዶች ላይ የገንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እየሰራ መሆኑን መገንዘብ የተቻለ ቢሆንም በክትትል ኦዲቱ ወቅት  በአካል የታዩ መናሀሪያዎች የአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ የአዲስ አበባ መለስተኛና አነስተኛ፣አስኮ፣ቃሊቲና አዳማ መናሀሪያዎች ወጥ በሆነ ሁኔታ ተግብረው አለመገኘታቸው የክትትልና ቁጥጥር ማነስ ችግር መኖሩን ያመለክታል፡፡

**የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ የሥራ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርቶችን ለባለስልጣኑ መ/ቤት የሚያቀርብ መሆኑን በተመለከተ**

71. በክዋኔ ኦዲቱ የተገኘው ግኝት፤ ባለስልጣን መ/ቤቱ የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በተሰጠው ውክልና መሰረት መሥራቱን እና በየጊዜው የሥራ አፈፃፀምና የፋይናንስ

ሪፖርቶች አቅርቦ የማያውቅና የቅርንጫፉም ሂሳብ በባለሥልጣኑ አመታዊ ሂሳብ መግለጫ ላይ የማይካተት መሆኑን ነው፡፡

72. በከዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ ተግባራዊ ባለመደረጉ በክትትል ኦዲቱ ወቅትም የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ የሥራ አፈፃፀም እና የፋይናንስ ሪፖርቶችን ለባለስልጣን መ/ቤቱ የማይልክ መሆኑ ታውቋል፡፡

73. ስለ ጉዳዩ የትራንስፖርት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ የሥራ አፈፃፀም እና የፋይናንስ ሪፖርት የማያቀርብበትን ምክንያት በግልፅ የማያውቁ መሆኑን ነው፡፡

74. ስለ ሁኔታው የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ የትራንስፖርት ኦፕሬሽን ዋና የሥራ ሂደት መሪ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የአዲስ አበባ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ከ 2004 ዓ.ም ጀምሮ ባለስልጣኑ በሰጠው ውክልና በቢሮ ደረጃ ሲቋቋም ተጠሪነቱ ለከተማው አስተዳደር በመሆኑ የሩብ፣ የመንፈቅና ዓመታዊ ሪፖርቶች የሚደረጉት ለዚሁ አካል በመሆኑ፤ ሆኖም ግን በዓመት አንድ ጊዜ በሚደረግ የምክክር ጉባኤ ለአጠቃላይ ሪፖርት ግብዓት የሚሆኑ ልዩ ሪፖርት ከማቅረብ የዘለለ የሪፖርት ግንኙነት ያልተደረገ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

75. ባለስልጣን መ/ቤቱ በቁጥር ትባ/ዋዳ/287/11/02 ቀን 15/11/02 በተፃፈ ደብዳቤ ለአዲስ አበባ ውክልና በሰጠው መሰረት በአግባቡ እየተሰራ መሆኑን አለመከታተሉ በአዋጅ የተሰተውን ኃላፊነት እየተወጣ መሆኑን አዳጋች ያደርገዋል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

ባለስልጣን መ/ቤቱ ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣ የተሟላ እና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት እንቅፋት የሆኑ የአሰራር ድክመቶችን ያሉበት መሆኑን በ 2005/2006 ዓ.ም በተደረገው የክዋኔ ኦዲት ከተገለፁት በመጠኑ የተቀረፉ ቢሆንም በክትትል ኦዲቱ ወቅትም አፅንዖት ተሰጥቷቸው መወገድ የሚገባቸው ችግሮች ያሉ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እነርሱም ዋና ዋናዎቹ፡-

76. በአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ሚኒባስ ታክሲዎች እና ድጋፍ ሰጪ ሚኒባሶች ከተፈቀደላቸው የወንበር ቁጥር በላይ ጨምረው ተሳፋሪ የሚጭኑ መሆኑ፣
77. የባለስልጣኑ መ/ቤት የድሬዳዋ ቅርንጫፍ መናህሪያ መጠናቀቅ ከሚገባው ጊዜ በ 11 ወራት ዘግይቶ የተጠናቀቀ መሆኑ፣
78. የአየር ጤና መናህሪያ በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት በታየው ችግር ምክንያት እስካሁን ሥራ አለመጀመሩ፣
79. የቃሊቲ መናህሪያ ደረጃውን ጠብቆ የተገነባ ባለመሆኑ ለተሽከርካሪዎች እና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ምቹ የአገልግሎት ሥፍራ የሌለው መሆኑ፣
80. የአዲስ አበባ አገር አቋራጭና አዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ መነሀሪያዎች ረጅም የአገልግሎት ዘመን የሰጡ በመሆናቸው የአገልግሎት አሰጣጣታቸው በቂ አለመሆኑ፣
81. በናሙና በታዩ በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ በአዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ፣ በአስኮ፣ላም በረትና ቃሊቲ መናህሪያዎች ግቢ ውስጥ የሰርቪስ ጊዜያቸው በ 3 ዓመት ያለፈ የእሳት አደጋ መከላከያዎች የተገኙ ሲሆን፣በአዳማ ከተማ መናህሪያ ግቢ ውስጥ የሌለ መሆኑ፣
82. የአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ፣ላም በረት፣ ቃሊቲ፣ አስኮና የአዳማ ከተማ መናህሪያዎች የጠፉ ንብረቶች ማቆያ በግልፅ ቦታ በሚታይ መልኩ የሌላቸው ሲሆን፤እንዲሁም ደረጃቸውን የጠበቁ መፀዳጃ ቤቶች የአካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ የሌላቸው መሆኑ፣
83. የአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ አዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ እና አስኮ መናህሪያዎች የመንገደኞች ማረፊያና መጠበቂያ ከመቀመጫ ጋር ያላዘጋጁ ሲሆን፤

በአዳማ ከተማ መናሀሪያ የመንገደኞች መጠለያ የተዘጋጀ ቢሆንም መቀመጫዎች የሌሉት መሆኑ፣

84. በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣በአዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ፣አስኮ፣ ቃሊቲና አዳማ ከተማ መናሀሪያዎች ተሳፋሪዎች ወደ መናሀሪያ ሲገቡ ስለ አገልግሎት አሰጣጡ መረጃ የሚያገኙት በ/ማይክሮፎን/ ድምፅ ማጉያ ሲሆን፣ ኤሌክትሪካል ቢል ቦርድ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

85. ለአቅመ ደካሞችና ለአካል ጉዳተኞች የተለየ መግቢያ በር እና ዕቃዎቻቸውን በጋሪ የሚገፉባቸው የተለዩ በሮች በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ መናሀሪያ ብቻ የተዘጋጁ ሲሆን፣በሌሎቹ በናሙና በታዩ መናሀሪያዎች ያልተዘጋጁ መሆኑ፣

86. በአስኮ መናሀሪያ ውስጥ ለቢሮዎች ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ መብራት ቢኖርም በግቢው ውስጥ አገልግሎት የሚሰጥ መብራት የሌለ መሆኑ፣እንዲሁም በሁሉም በናሙና በታዩ መናሀሪያዎች ለተሳፋሪ ለመጠጥ አገልግሎት የሚውል ውሃ በተለየ ሥፍራ የተዘጋጀ የሌለ መሆኑ፣

87. በናሙና በታዩ ለህዝብ አገልግሎት ለመስጠት የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች በአዲስ አበባ መለስተኛና አነስተኛና አስኮ መናሀሪያዎች የሚጓዙበትን መስመርና ታሪፍ ተሳፋሪው ሊመለከተው በሚችለው ሥፍራ ለጥፈው ያልታዩ መሆኑ፣

88. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የከተማ አገልግሎት የሚሰጡ ታክሲዎች ታሪፍ ለጥፈው ያልታዩ ሲሆን፤የስምሪት መስመሮችን እርቀትና የሚያስከፍሉትን ዋጋ የሚያሳዩ ሰሌዳዎች ከየቦታው የተነሱ መሆኑ፣

89. በናሙና በታዩ በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ በአዲስ ከተማ መለስተኛና አነስተኛ፣ በላም በረት፣አስኮ፣ ቃሊቲና አዳማ ከተማ መናሀሪያዎች ከአገር አቋራጭ እና አብዛኛው መለስተኛ ተሽከርካሪዎች ለደረጃቸው የተፈቀደውን ቀለም የቀቡ ሲሆን፤ አነስተኞቹ ሚኒባስ ተሽከርካሪዎች ለየደረጃቸው ተፈቀደውን ቀለም ያልቀቡ መሆኑ፣

90. በናሙና ተመርጠው በታዩት በሁሉም መናሀሪያዎች አሽከርካሪዎችና ረዳቶቻቸው በየደረጃው የሚፈቀደውን የደንብ ልብስ አሟልተው ያልተገኙ መሆኑ፤ እንዲሁም በተሽከርካሪዎች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ መጋረጃዎችን በንፅህና የማይዙ መሆኑ፤

91. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአገር አቀፍ ደረጃ የፍጥነት ወሰን መመሪያን ወቅታዊ አለማድረጉ፣

92. የሌሊት ህገ ወጥ ስምሪትን ለመግታት በቅንጅት ሥራ ጥረት የሚደረግ ቢሆንም የትራፊክ ኬላዎች ከየቦታው እንዲነሱ በመደረጋቸው የሚቆጣጠር አካል ባለመኖሩ ሥራው አዳጋች እየሆነ መምጣቱ፣

93. ሰሌዳቸው በሚመለከተው አካል የተፈቱ ተሽከርካሪዎች ስምሪት የማይሰጣቸው ቢሆንም፤ ተሽከርካሪዎቹን ከመቆጣጠር አንፃር ወጥ አሰራር የሌለ መሆኑ፣

94. ዓርማ የሌላቸው እና ደረጃ ያልተሰጣቸው ኮድ 3 ሰሌዳ ያላቸው በአዲስ አበባ ውስጥ ለህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ድጋፍ የሚሰጡ ሚኒባሶች መኖራቸው፣

95. የባለስልጣኑ መ/ቤት የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያልተደገፈ መሆኑ፣

96. የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ የሥራ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርቶች ለባለስልጣኑ መ/ቤት የማይቀርቡ መሆኑ፣

97. ባለስልጣኑ መ/ቤት የአፈፃፀም መመሪያ ተግባራዊ በማያደርጉ መ/ቤቶች ላይ በጋራ መድረክ ውይይት ወቅት ግፊት ከማድረግ ውጪ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር በተለየ መልኩ ያቀረበበት ሁኔታ ያለመኖሩ፣

# ክፍል አራት

## በክትትል ኦዲት(Follow up audit) የታዩ ትኩረት የሚሹ የማሻሻያ ሀሳቦች

በ2005/2006 ዓ.ም በባለስልጣኑ መ/ቤት በህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር ላይ ለባለስልጣኑ መ/ቤት በቀረበ ሪፖርት ላይ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች የተወሰኑት ተግባራዊ የተደረጉ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ተግባራዊ ያልተደረጉ በመሆናቸው ባለስልጣን መ/ቤቱ የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲተገበሩ እንዲያደርግ በድጋሚ የሚከተሉት የማሻሻያ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

98. ባለስልጣኑ መ/ቤት ከአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ ጋር በቅንጅት በመስራት የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ሚኒባስ ታክሲዎችንና ድጋፍ ሰጪ ሚኒባሶችን ከተፈቀደላቸው ወንበር በላይ እንዳይጭኑ፣መስመር እንዳይቆራርጡ እና ከታሪፍ በላይ እንዳያስከፍሉ እንዲሁም ታሪፍን በግልፅ ቦታ እንዲለጥፉ ሊያስደርግ ይገባል፡፡
99. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአየር ጤና አካባቢ የተሰራው መናህሪያ ሥራው ተጠናቆ ለህዝብ አገልግሎት እንዲውል ሊያደርግ፤እንዲሁም የቃሊቲ መናህሪያ ደረጃውን ጠብቆ እንዲሰራ በማድረግ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፡፡
100. ባለስልጣን መ/ቤቱ በመናህሪያ ግቢ ውስጥ መገኘት የሚገባቸውን መሰረታዊ የአገልግሎት መስጫዎች የእሳት አደጋ መከላከያ፤ ለአቅመ ደካሞችና ለአካል ጉዳተኞች መግቢያ የሚያገለግል የተለየ በር፣ ለአካል ጉዳተኞች የሚያገለግል ዊል ቸር፣ ደረጃውን የጠበቀ መፀዳጃ አካል ጉዳተኞችንም ታሳቢ ያደረገ፣ የዕቃ መመዘኛ ሚዛን፣ የዕቃ መግፊያ ጋሪዎች እና ሸኚ የማይገባባቸው ዕቃዎች በጋሪ የሚገቡባቸው የተለዩ መግቢያ በሮች፣ተሳፋሪዎች ሊጠለሉባቸው የሚችሉበት መቀመጫ ያላቸው ቦታዎች፣ ለመጠጥ አገልግሎት የሚውል ውሃ በተለየ ቦታ የተዘጋጀ፣ ለተሳፋሪው ስለትራንስፖርት አገልግሎት መረጃ መስጫ ኤሌክትሮኒክስ ቢል ቦርድ እና ኢንፎርሜሽን ዴስክ እና የጠፉ ንብረቶች ማቆያ/ለጥቃቅን/ በግልፅ ቦታ የተቀመጡ መኖራቸው ተሟልተው መገኘታቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡
101. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአስኮ መናህሪያ ግቢ ውስጥ ለጥበቃ አገልግሎት አመቺነት የመብራት አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ አለበት፡፡

102. ባለስልጣን መ/ቤቱ አንዳንድ መለስተኛ ተሽከርካሪዎችንና ሁሉንም አነስተኛ ተሽከርካሪዎችን ለደረጃቸው የተፈቀደውን ቀለም ቀብተው መንቀሳቀሳቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

103. ባለስልጣን መ/ቤቱ አሽከርካሪዎችና ረዳቶቻቸው በየደረጃቸው ለሚያሽከረክሩአቸው የተፈቀደውን የደንብ ልብስ እንዲለብሱ፤ እንዲሁም በተሽከርካሪዎቻቸው ውስጥ የሚጠቀሙአቸውን መጋረጃዎች በንፅህና እንዲጠብቁ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርጉ ይገባል፡፤

104. ባለስልጣን መ/ቤቱ በ 1961ዓ.ም የወጣውን የፍጥነት ወሰን መመሪያ ወቅታዊ ማድረግ አለበት፡፡

105. የሌሊት ህገ ወጥ ስምሪትን ለመከላከል ባለስልጣን መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

106. ሰሌዳቸው በሚመለከተው አካል የተፈቱ ተሽከርካሪዎች ቅጣታቸውን እስኪሽፍኑ በመናሀሪያ ውስጥ ለቁጥጥር እንዲያመች የሚቆዩበት ወጥ አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡

107. ደረጃ ያልተሰጣቸው ኮድ 3 ያላቸው በአዲስ አበባ ውስጥ በትራንስፖርት ድጋፍ ሰጪነት የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች ለቁጥጥር አመቺነት ተለይተው የሚታወቁበት የአሰራር ስርዓት በባለስልጣኑ መ/ቤት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

108. ባለስልጣኑ መ/ቤት የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓቱን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ማድረግ አለበት፡፡

109. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮን የሥራ አፈፃፀም እና የፋይናንስ ሪፖርት ሊከታተል ይገባል፡፡

110. ባለስልጣኑ መ/ቤት የአፈፃፀም መመሪያ ተግባራዊ ስለማያደርጉ መ/ቤቶች ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ጉዳዩን የሚያቀርብበት አሰራር ሊኖረው ይገባል፡፡

# አባሪ 1

## በህዝብ ትራንስፖርት የክዋኔ ኦዲር ሪፖርት የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ እና ከክልሎች ጋር በመተባበር የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጡን ተደራሽ፣ ደህንነቱን ጥራቱንና ምቾቱን የጠበቀ ለማድረግ የሚያስችለውን የአሰራር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ለህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውል መናኸሪያ ቦታ መረጣ እና ግንባታ ሲደረግ ባለስልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን መስፈርት ተግባራዊ መሆኑን ሊያረጋግጥና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ በሥራ ላይ ያሉ መናኸሪያችም መስፈርቱን አሟልተው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ አለበት፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የድሬዳዋ መናኸሪያ ግንባታ በፍጥነት እንዲጠናቀቅ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሰረት የህዝብ ትራንስፖርት የመናኸሪያ አገልግሎት አሰጣጥ ተግባራዊ መደረጉን ሊያረጋግጥና ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች በተሰጣቸው ስምሪትና ታሪፍ መሰረት አገልግሎት መስጠታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአየርጤና አካባቢ የተሰራው መናኸሪያ ለሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በሚያመች መልኩ መንገዱ ተስተካክሎ ወደ ሥራ እንዲገባ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ማመላለሻዎች ከውጪ ሲገቡም ሆነ አገር ውስጥ ተቀጥቅጠው ሲሰሩ ተሽከርካሪዎች ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡ አሁን በሥራ ላይ ያሉትን አመቺ ለማድረግ የተዘጋጀው ዲዛይን በፍጥነት ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ አለበት፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው የሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ደረጃ የተሰጣቸው መለስተኛና አነስተኛ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በሙሉ ለደረጃው የተቀመጠውን ቀለም መቀባታቸውን የሚያረጋግጥበትን የአሠራር

ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግና ይህን ተግባራዊ ባላደረጉ ላይ እርምጃ መውሰድ ይገባዋል፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ተሸከርካሪዎችን ብቃት በመለየት አስገዳጅ ናቸው ተብሎ በየደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት አሟልተው በየደረጃቸው መስራታቸውን አሽከርካሪዎቹም ሆኑ ረዳቶች በወጣው መስፈርት መሰረት ለደረጃው የሚገባውን የደንብ ልብስ መልበሳቸውን ሊያረጋግጥ ይገባዋል፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ በአገር አቀፍ ደረጃ ከ45 ዓመት በፊት የወጣውን የፍጥነት ወሰን መመሪያ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር ወቅታዊ ማድረግ እና በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተልና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ በቀን እና በሌሊት የሚፈፀሙ ሕገወጥ ስምሪትን ለማስቆም የወጡ ደንቦችና የአሰራር መመሪያዎች በአገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም ክልሎችና የባለድርሻ አካላት ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተልና ሊቆጣጠር እንዲሁም ሁሉንም ክልሎች በማስተባበር ወጥና ቀጣይነት ያለው ቅንጅታዊ የአሠራር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን የስምሪት አፈፃፀም መመሪያ በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሚመለከተው አካል የኋላ ሰሌዳቸው የተፈቱ ተሽከርካሪዎች ከመናኸሪያ የስምሪት ፈቃድ እንዳይሰጣቸው፣ ሰሌዳቸው ተፈቶ በመንገድ ላይ እንዳይንቀሳቀሱ የሚያደርግበትን እና እርምጃ የሚወሰድበትን የአሰራር ስርዓት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- የሕዝብ ማመላለሻ ፈቃድ የተሰጣቸው ደረጃቸውና የማህበራቸው ዓርማ ለተመልካች በሚታይና በተወሰነ ሥፍራ ብቻ የሚለጥፉበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ሕገወጥ የትራንስፖርት ስምሪትን ለመከላከል በባለሥልጣኑም ሆነ በክልሎች ለሌላ ንግድ ሥራ ኮድ 3 የሚሰጣቸው ሚኒባሶች ፈቃድ የጠየቁበትን የንግድ ድርጅት ዓርማ የሚገልጽ ለተቆጣጣሪዎችም ሆነ

ለሌላው በሚታይ ሥፍራ ላይ የሚለጥፉበትን የአሰራር ሥርዓት ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ ለትራንስፖርት መረጃ አያያዝ የሚሰጠው ትኩረት በማሳደግና አገር አቀፍ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርአት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ አስተማማኝ ጥራት ያለውና ወቅታዊ መረጃ በተሟላ መልኩ ሊይዝ ይገባል፡፡
- በባለሥልጣን መ/ቤቱ በወጡ የህዝብ ትራንስፖርት ደንቦች መመሪያዎች፣ መለኪያ መስፈርቶች፣ ስታንዳርዶች ፣ የተለያዩ ጥናቶች ፣ የስራ እቅዶች የመሳሰሉትን ላይ ለክልል ትራንስፖርት ቢሮዎችም ሆነ ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ በተጠናከረ መልኩ ሊሰጥና ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በተሰጠው ውክልና መሰረት መስራቱን እና በየጊዜው የስራ አፈጻጸም እና የፋይናንስ ሪፖርቶች ማቅርቡን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡